Är du utsatt för våld i en nära relation? - Amhariska

# በቅርብ ዝምድና መሓል ለአመጽ ጎይል ተዳርገዋልን?

በቅርብ ዝምድና መሓል ያለ የአመጽ ጎይል የተላያየ መልክ ሊኖረው ይችላል። ኣንዳንድ ጊዜ ነውጠኛው የኑሮ ጓደኛ ሊሆን ይችላል፥ አንዳንዴ ደግሞ የሥጋ ዘመድ። ወላጆቻቸውን ነውጥ ወይም ለአመጽ ጎይል የሚዳርጉ ልጆችም ኣሉ። ነውጡ በዓካል ወይም በኣዕምሮ ላይ ጉዳት ማድረስ፥ እንዲሁም በግብረ ሥጋ መድፈር ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል፥ አንድ ሰው

- በፀያፍ ቃል ከጠራዎት ወይም መጥፎ ስድብ ከሰደበዎት ወይም ደካማና መንቻካ እንደሆኑ እንዲሰማዎት ካደረገ
- ከገፈተሮት፥ ከመታዎት፥ ከቀላዎት ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ ጉዳት ካደረሰቦት፥
- ከተቆጣጠሮት ወይም ካገቶት፥ የማይፈልጉትን እንዲያደርጉ ካስገደዶዎት
- ኣመለካከትዎን ወይም የኣኗኗር ዘይቤዎን እንዲለውጡ ካስገደድዎት
- ግብረ ሥጋዊ ለሆነ ግንኙነት ካስገደድዎት
- በራስዎ ገንዘብ ላይ የገንዘብ ኣያያዝዎን የሚቆጣጠርዎ ከሆነ፥

ለነውጥ ተዳርገዋል ማለት ይቻላል።

**ጥበቃና ድጋፍ የማግኘት መብት ኣሎት**

ማንም ሰው በቅርብ ዘመዱ ለሚሰነዘርበት ነውጥ ሰለባ ሊሆን ይችላል። እርሶም ለዚህ ዓይነቱ ጥቃት የተጋለጡ ከሆነ መረጃ፥ ጥበቃና ድጋፍ ያገኛሉ፥ እንዲሁም ከበሬታና ልባዊ ጎዘኔታ የተሞላበት መስተንግዶ ይደረግሎታል። ይህ መብትዎ ነው። ልጅ ካልዎትም፥ ልጅዎ ጭምር ድጋፍ የማግኘት መብት ኣለው/ኣላት።

የሚከተሉትን ዓይነቶች ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ፥

- ውይይታዊ ድጋፍ
- ጥበቃና ጊዚያዊ መኖሪያ ቤት
- የኢኮኖሚ ድጋፍ
- ከባለሥልጣናትን ለምሳሌ ፖሊስ የማግኘት ድጋፍ፥

እንድንረዳዎት ያግኙን። ከፈለጉ ማንነትዎን ሳያሳውቁ ሊገናኙን ይችላሉ።

ለአስቸኳይ ጊዜ ሁሌም 112 ይደውሉ።

**ከእነዚህ ጋር ግንኙነት ያድርጉ፥**

- **ሥራው/ኀላፊነቱ:** Vuxenenhetens mottagningsgrupp
- **ስልክ ቁጥር:** 08-58169000
- **ድረገጽ:** www.upplands-bro.se
- **ኣድራሻ:** Furuhällsplan 1, Kungsängen

**Andra i kommunen som erbjuder stöd - Amhariska**

# በኮሚዩኑ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ድጋፍ ሰጪዎች

ኮሚዩን ውስጥ ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ ተቋማት አድራሻ እዚህ ማግኘት ትችላለህ/ሽ። ለምሳሌ የጤና ጣቢያ፥ የሴቶች ድጋፍ ሰጭና የወንጀል ተጠቂዎች ድጋፍ ሰጭ ናቸው።

- **ሥራው/ኃላፊነቱ:** Kvinnojouren Anna
- **ኢሜል:** info@kvinnojourenanna.se
- **ስልክ ቁጥር:** 08-58240999
- **ድረገጽ:** www.kvinnojourenanna.se

**Nationellt stöd - Amhariska**

# ኣገር ኣቀፍ ድጋፍ

### Kvinnofridslinjen 020-50 50 50

ዛቻና ነውጥ ላሳለፉችሁ ኣገር ዓቀፍ የስልክ ድጋፍ። ስዊድንኛ የማይችሉ ቢሆንም መናገር ይችላሉ። ጥሪው ነፃ ብቻ ሳይሆን የጥሪ ቆጣሪ ሂሳብ ዝርዝር ላይ ጥሪው መደረጉ ራሱ ጭርሶ ኣይወጣም። ማንነትዎን ሳይገልጹ መደወል ይችላሉ።

www.kvinnofridslinjen.se

### BRIS 116 110

ወጣቶች ድጋፍ የሚያገኙበት መስመር። በጽሁፍ ሓሳብ ወዲያው መለዋወጥና (chatta) በኢሜል መገናኘት ይቻላል። ማንነትህ/ሽ ሳይገለጽ መገናኘት ይቻላል።

www.bris.se

### RFSL:s brottsofferjour 020-34 13 16

በወሲባዊ ማንነታችሁ ለወንጀል ጥቃት ወይም ለነውጥ ለተጋለጣችሁ የስልክ ድጋፍ መስመር።

www.rfsl.se/brottsoffer/

### Terrafem 020- 52 10 10

ለነውጥ የተጋለጣችሁ የስልክ ድጋፍ መስመር። በተለያዩ ቋንቋዎች ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። ጥሪው ነፃ ብቻ ሳይሆን የስልክ ሂሳብ ዝርዝር ላይ ጥሪው መደረጉ ጭርሶ ኣይወጣም። ማንነትዎን ሳይገልጹ መደወል ይችላሉ።

www.terrafem.org

### Brottsofferjouren 0200-21 20 19

ለወንጀል የተጋለጡ የስልክ ድጋፍ መስመር። ስዊድንኛ የማይችሉ ቢሆንም መደወል ይችላሉ።

www.boj.se